
በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ነሐሴ /2017 ዓ.ም







እንኳን ለነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የልደት በዓል (መውሊድ) በሠላም አደረሰዎ!

ማውጫ

የንግድ ምህዳር በዶ/ር ካሳሁን ጎፌ————————1
የኢትዮጵያን ይግዙ የንግድ ኤክስፖ————————-1
የአዲስ ዓመት የፕሬዚዳንቱ መልዕክት————-2
የግድብ መጠናቀቅ የፕሬዚዳንቱ መልዕክት——-2
የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ምክክር መድረክ——3-4
ፕሬዚዳንቱ ከኢንዶኔዥያ አምባሳደር ጋር——-—4
የምክር ቤቱ ሰራተኞች ስብሰባ በአዳማ————5
ፕሬዚዳንቱ ከኢዜአ ጋር ያደረጉት ቆይታ————6
ኢትዮ-ኮሎምቢያ ቢዝነስ ፎረም————————6
4ኛው የአፍሪካ ንግድ ትርኢት በአልጀርስ—-——7
ከአልጀሪያ የንግድ ም/ቤት ፕረዜዳንት ጋር——-8
ከSNV ጋር ስምምነት ፊርማ————————9
ከአፍሪካ ኢንሞሽን ጋር ስምምነት ————————9
ውይይት ከኮሎምቢያ አምባሳደር ጋር————10
ኤግዚቢሽን በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች———10
በቴክኒክና ሙያ ዙሪያ ውይይት————————-11
ከኦማን ኩባንያዎች ጋር ውይይት————————12
ከኦሮ ኮንስትራክሽን ኃላፊ ጋር ውይይት———12
ከቦልድ ሶሉሽን ግሩፕ ተወካች ጋር ውይይት——13
የአዲስ አመት ኤግዚቢሽን በሐዋሳ————————13
PPD በመቐለ ከተማ መካሄድ————————-14
የአምባሳደሮች የእርባምንጭ ከተማ ——-14
ስምምነት በተደረገባቸው ምክክሮች———15
የበሻሻ ንግድ ምክር ቤት በጎ ስራ————-16

የንግድ ምህዳሩን ምቹ የሚያደርጉ ተግባራት በዘላቂነት ተጠናክረው ይቀጥላሉ:- የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዶክተር ካሣሁን ጎፌ።





"የኢትዮጵያን ይግዙ" የንግድ ሳምንት ኤክስፖ 2017 በጀት ዓመት መገናኛ አካባቢ በሚገኘው የጥራት መንደር ውስጥ እየተካሄደ ሲሆን እስከ ነሐሴ 29 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል።

ከኤስፖው ጎን ለጎን የሀገር ውስጥ ንግድን ህጋዊነትና ተደራሽነት ከማረጋገጥ በተጓዳኝ ማዘመን ላይ ትኩረት ያደረገ የፓናል ውይይት እየተካሄደ ነው።



የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በወቅቱ እንዳሉት፤ የንግድ ምህዳሩን ለሸማቾች እና ንግዱ ማህበረሰብ ምቹ ለማድረግ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል።

በዚህም የሸማች እና የንግዲ ማህበረሰብ እርካታ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እያደገ መምጣቱን ጠቁመው፤ በቀጣይነትም ተጠናክረው መቀጠል እንዳለበት አንስተዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 3 ነጥብ 25 ሚሊዮን ተገልጋዮች የኦንላይን ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መሰጠቱን ተናግረዋል።

ለገበያ መሰረተ ልማት መስፋፋት ትኩረት መሰጠቱን የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ ገበያውን ለማረጋጋት ከፍ ያለ ፋይዳ ያላቸው በርካታ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉንም አመልክተዋል። ሚኒስትሩ እንዳሉት፣ ከህግና ስርዓት ውጪ በሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች ላይም የሚወሰደው እርምጃ መቀጠሉን ተናግረዋል።

ለአብነትም በ2017 በጀት ዓመት 110 ሺህ ህገ ወጥ ድርጊት የፈጸሙ ነጋዴዎች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ መወሰዱን በመጥቀስ።

የንግዱን ዘርፍ ምቹ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ገልጸው፤ መሰል የውይይት መድረክ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማመላከት የላቀ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል።

የፓናል ውይይቱ በቀጣይ ሶስት ቀናትም በጥራት መሠረተ ልማት፣ በወጪ ንግድና በኢ-ኮሜርስ ንድፎችና ተግባራት ላይ አተኩሮ ይቀጥላል።(ምንጭ ን/ቀ/ት/ሚ)

የኢትዮጵያን ይግዙ የንግድ ሳምንት ኤክስፖ በኢፌዴሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስተባባሪነት በጥራት መንደር ተካሄደ።

ከዚሁ ጋራ ተያይዞም የሀገር ውስጥ ንግድ የፓናል ውይይት እየተካሄደ ሲሆን፤ በውይይት መድረኩም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢርን ጨምሮ ከተለያዩ ተቋማት የተወጣጡ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል ።



የፓናል ውይይቱን በንግግር የከፈቱት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዶ/ር ካሣሁን ጎፌ ሲሆኑ ከውይይቱ አቅጣጫ አመላካችና መፍትሔ ጠቋሚ ሐሳቦች እንደሚነሱና ይህም አጠቃላይ የንግድ ስርዓቱን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ እንደሚያግዝ ገልፀዋል ።

የፓናል ውይይቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር አብዱልሃኪም ሙሉ እየመሩት ሲሆን በፓናሊስትነትም የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ሶፍያ ካሣ ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የስራ ኃላፊዎች ተሳትፈዉበታል።





በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ በንግዱ ማኅበረሰብ፤ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አንዲሁም በራሴ ስም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ደስ አላችሁ! ለማለት እወዳለሁ ።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግሉን ዘርፍ በመወከል በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ የተሰማውን ላቅ ያለ ደስታ በድጋሜ እየገለጸ በግንባታው ሂደት ከጅማሮው እስከ ፍጻሜው ድረስ የንግዱ ማኅበረሰብ ከመንግስት ጋር እጅና ጓንት በመሆን ላደረገው ርብርብ ምስጋናውን ያቀርባል።

ግድቡ ሀገር ወደብልጽግና እንድትሸጋገር እንዲሁም የኢትዮጵያውያን ኑሮ እንዲሻሻል የሚደርገውን ጥረት ላቅ ወዳለ ደረጃ የሚያደርሰው ከመሆኑም ባሻገር ፤ በዓለም አደባባይ ሀገራችን ከፍ ብላ እንድትታይ ያደረገ የአሸናፊነት ምልክታችን ነው።

በመሆኑም ፣ በታላቁ ህዳሴ ግድብ ያስመዘገብነውን የጋራ ስኬት በሌሎች የልማት ስራዎቻችንም ለመድገም ቃል የምንገባ ይሆናል።

ምክር ቤታችንም ለመላው የሀገራችን ህዝቦች እና የንግዱ ማኅበረሰብ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ይወዳል። አመሰግናለሁ።

ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር
የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እና የንግዱ ማኅበረሰብ እንኳን ለ2018 አዲስ ዓመት በሰላምና በጤና አደረሳችሁ!

ዓመቱ የሰላምና የብልጽግና እንዲሁም የስኬት ዓመት እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በሀገራችን የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ሚና በሚፈለገው ደረጃ እንዲደርስ፤ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና የመላው ህዝባችን ኑሮ ተሻሽሎ የምንፈልገውን ልማትና ብልፅግና ማረጋገጥ እንዲቻለን በግሉ ዘርፍ አቅም ግንባታ፣ በምርምርና ፖሊሲ አድቮኬሲ እንዲሁም በስልጠና እና አረንጓዴ ልማት የሚጠበቅበትን ሁሉ እያደረገ ይገኛል።

ካለፈው አመት ጀምሮም አጠቃላይ የተቋም ሪፎርም ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ በአዲስ አሰራርና አደረጃጀት የኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎቶች እንዲተዋወቁ፣ የንግዱ ማኅበረሰብ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆንና ምቹ የቢዝነስ ከባቢ እንዲፈጠር ከመቼውም ጊዜ በላይ እየሰራን እንገኛለን።

አዲሱ ዓመት መላው የንግዱ ማኅበረሰብ እንዲሁም አባል ምክር ቤቶች በትብብርና አንድነት መንፈስ በመስራት የበለጠ ውጤት የምናስመዘግብበት የስኬትና የብልጽግና ዓመት እንዲሆን እመኛለሁ። አመሰግናለሁ!

ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት

በአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያ የሆነው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የኤሌክትሮኒክ የምክክር መድረክ (Electronic public private dialogue) የማስጀመሪያ መርሀ ግብር ተካሄደ።





በማስጀመሪያ መርሃ ግብሩም የኢፌዴሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አብዱልሀኪም ሙሉ ፤ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆብር፣ የምክር ቤቱ የቦርድ አባላት እንዲሁም የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ተገኝተዋል።

በአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያ የሆነው ይህ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የኤሌክትሮኒክ የምክክር (Electronic public private dialogue (EPPD) መድረክ ባለድርሻ አካላት ያሏቸውን ጥያቄዎችና የፖሊሲ ግብዓቶችን በቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለመንግስት አካላት የሚያደርሱበትና ተገቢው ምላሽ የሚሰጥበት ዲጂታል አሰራር ነው።



ፕሮጀክቱ የግሉን ዘርፍ ወጪና ጊዜን ከመቆጠቡም ባሻገር ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚደረገዉ ጥረት አካል መሆኑን የጠቀሱት የምክር ቤቱ ዋና ፀሃፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ የግሉ ዘርፍ ይህንን ፕላትፎርም በመጠቀም ያለዉን ለፖሊሲ ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳብ እና ስተያየቶችን እንዲሁም ጥያቄዎችን እንዲያቀርብ ጥሪ አቅርበዋል።

ኤሌክትሮኒክ የምክክር መድረክ የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት እና የመንግስት ተቋማት ተቀራርበው እንዲሰሩ የሚያደርግ የፖሊሲ ግብዓት ለማግኘት የሚያግዝ መንግስትና የግሉን ዘርፍ መተማመንን የሚያመጣ መሆኑ በመርሀ ግብሩ ላይ ተነስቷል።

ከግሉ ዘርፍ ለሚነሱ ጥያቄዎች የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትም ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸውም ዶክተር ኣብዱልሀኪም ሙሉ ገልጸዋል።







የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የኤሌክትሮኒክ የምክክር መድረክ (Electronic public private dialogue) በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል መተማመን የሚፈጥር መሆኑ ተገለጸ።



(Electronic public private dialogue (EPPD) ዲጂታል ኢትዮጵያን እዉን አይነተኛ መሳሪያ መሆኑን ገልጸዋል።

የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላትም የዲጂታል አሰራሩን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባቸውና የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትም አስፈላጊውን ምላሽ በመስጠት አሰራሩን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባቸው ተነስቷል።

የዲጂታል ምክክር መድረኩ አገልግሎት ፈላጊው ባለበት ሆኖ በቀላሉ ሀሳብ እንዲሁም ግብዓት የሚሰጥበት መሆኑ በማስመጀመሪያ መርሀግብሩ በተካሄደ ውይይት ላይ ተነስቷል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አብዱልሀኪም ሙሉ ፤ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆብር፣ የምክር ቤቱ የቦርድ አባላት እንዲሁም የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች በተገኙበት በተካሄደ ውይይት በተለይም ከቋንቋ ብዝሀነት፣ ከኢንተርኔት አቅርቦት እና ከአጠቃቀም ጋር የተያያዙ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን መፍታት እንደሚገባ ተነስቷል።

በአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያ የሆነው ይህ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የኤሌክትሮኒክ የምክክር ለማድረግ



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆብር በኢትዮጵያ ከኢንዶኔዥያ ሪፐብሊክ አምባሳደር ፋይዘል ቸሪ ሲዳርታ ጋር ተወያዩ።



በውይይታቸውም የኢትዮጵያንና የኢንዶኔዥያን ንግድና ኢንቨሥትመንት ግንኙነት ማሣደግ በሚቻልባቸው የትብብር መስኮች ላይ መክረዋል።



ኢንዶኔዥያ እና ኢትዮጵያ ያላቸው የንግድ ልውውጥና የኢንቨሥትመንት መጠን እያደገ መምጣቱንና በኢትዮጵያም የኢንዶኔዥያ ኩባንያዎች በሥራ ላይ መሆናቸው በውይይቱ ተነስቷል።

ፕሬዚዳንቱ አቶ ሰብስብ አባፊራ ምክር ቤቱ በንግድና አድቮኬሲ እንዲሁም በሌሎች መሥኮች በሚያከናውናቸው ትስስር ለማሣድግ በሚችሉባቸው ተቋማዊ ጉዳዮች ዙሪያ

ኢንቨሥትመንት፣ በአቅም ግንባታ፣ በምርምርና ተግባራትና ከኢንዶኔዥያ ጋር ያለውን የቢዝነስ አብራርተውላቸዋል።



በኢትዮጵያ እየተካሄዱ ባሉ የኢኮኖሚ ለውጦች እና አገሪቷ ለ ው ጭ ባ ለ ሀ ብ ቶ ች ባሏት የኢንቨሥትመንት አማራጮች ላይ ማብራርያ የሰጧቸው አቶ ሰብስብ የኢንዶኔዥያ ባለሀብቶችም በ ኢ ት ዮ ጵ ያ ኢ ን ቨ ስ ት



እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል። አምባሳደር ፋይዘል ቸሪ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሀገር እየሆነች መምጣቷንና ኢንዶኔዥያም ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ለማሳደግ ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸዋል።በቀጣይ ጥቅምት ወር በጃካርታ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ ኤክስፖ ላይ የኢትዮጵያ የቢነዝነስ ተቋማት እንዲሣተፉም አምባሳደሩ ጥሪ አቅርበዋል።

ሠራተኞች በትብብር መንፈስ በመስራት ምክር ቤቱ የያዘውን ራዕይ ለማሳካት መስራት እንደሚጠበቅባቸው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለጹ።





ፕሬዚዳንቱ ይህንን ያሉት በምክር ቤቱ ዓመታዊ የሠራተኞች የሥራ አመራር ስብሰባ ላይ ተገኝተው የሥራ መመሪያ በሠጡበት ወቅት ነው።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለውን የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ላይ ሀገራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እየሠራ ሲሆን ውጤት እያመጣ ስለመሆኑም አንስተዋል።

ስለሆነም የምክር ቤቱ ሰራተኛ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የምክር ቤቱን ራእይ እና ተልእኮ በአግባቡ በመረዳት ለስኬታማነቱ በአንድነት መንፈስ መሥራት እንደሚገባውም ተናግረዋል።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና የጂ አይ ዜድ ቀጣናዊ የፋይናንስ ማናጀር ሙሀመድ አሊ ካሃን በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እና በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ ስምምነት ተፈራርመዋል።





በስምምነቱ ወቅት እንደተገለጸውም የፕሮጀክቱ እውን መሆን የሰለጠነና ብቃት ያለው የሰው ኃብት በማፍራት የቢዝነስ ዘርፉን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችል ነው።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና (TVET) ልዩ ትኩረት በመስጠት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዩኒት ያቋቋመ ሲሆን በፕሮጀክቱ ትግበራ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል። ፕሮጀክቱም ለ2 ዓመታት ተግባራዊ እንደሚደረግ በስምምነቱ ወቅት ተጠቅሷል።

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ዲጂታል ኢትዮጵያ የገበያ ትስስር በመፍጠርና ያልተገባ ወጪን በማስቀረት ለንግዱ ማህበረሰብ የተሳለጠ የመንግስት አገልግሎትእንዲያገኝ እያደረገ ስለመሆኑ ከኢዜአ ጋራ ባደረጉት ቆይታ ገልጸዋል።



ፕሬዚደንቱ አክለውም ፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ በገበያ ትስስር፣በጊዜ ቁጠባና ያልተገባ ወጪን በማስቀረት ለንግዱ ማህበረሰብ የተሳለጠ የመንግስት አገልግሎት እንዲያገኝ እያደረገ ነው።

ለመንግስት ሠራተኛው የደመወዝ ማሻሻያ መደረጉ በገበያ ላይ ምንም አይነት ችግር እንደማያመጣም ተገልጿል።

ፕሬዝዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በተጨማሪም ÷የንግድ ምክር ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት የሚያስችል ስትራቴጂክ ማሻሻያ መደረጉን አስታውቀዋል

የንግዱ ማህበረሰብም በሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ የሚያስችል ዝግጅት የሚያደርግበትን የማንቃትና የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል። የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራና ለዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት የንግዱን ማህበረሰብ የሚያዘጋጁ የግንዛቤ ማስጨበጫ የምክክር መድረኮች መፈጠራቸውን አንስተዋል።

መንግስት ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በሚያደርገው ጥረትም ምክር ቤቱ የንግዱን ማህበረሰብ አገልግሎቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀም እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል። የዲጂታል ኢትዮጵያ ሥርዓትም በገበያ ትስስር፣በጊዜ ቁጠባና ያልተገባ ወጪን በማስቀረት ለንግዱ ማህበረሰብ የተሳለጠ የመንግስት አገልግሎት እንዲያገኝ እያደረገ መሆኑን ተናግዋል። የንግድ ጤናማነትና የሕግ ተከባሪነት ሥርዓትን ለማስቀጠልም ከፌደራል እስከ ወረዳ ከሚገኙ ባለድርሻ ተቋማትና አካላት ጋር በትብብር እየተሰራ መሆኑን ገልዋል።

በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የንግድ ሥርዓት በተፈጠረበት ወቅት ለመንግስት ሠራተኛው የደመወዝ ማሻሻያ መደረጉም በገበያ ላይ ምንም አይነት ችግር አይመጣም ብለዋል። የኢትዮጵያን የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ እየተከናወኑ የሚገኙ ስኬታማ ተግባራትም በግብይት ምርት አቅርቦትና ፍላጎት ላይ አዎንታዊ ሚና እየተወጣ መሆኑን አንስተዋል። የመንግስት ሠራተኛን የደመወዝ ማሻሻያ ሰበብ በማድረግ በግብይት ወቅት ኢ-ምክንያታዊ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ አካላት ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሳቢ ይደረጋል ብለዋል።

የመንግስት ሠራተኛው የደመዝ ማሻሻያም በግብይት ሥርዓቱ ላይ ምንም አይነት ክፍተት የሚፈጥርበት ምክንያት እንደሌለ ተናግረዋል። የንግዱ ማህበረሰብም ከምንጊዜም በላይ ሸማቹን ህዝባቸውን በተገቢው ሁኔታ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት እንደሚጠበቅበት መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮ-ኮሎምቢያ የንግድና ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ ተካሄደ።





በፎረሙም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ያስሚን ወሃብረቢ፣ የኮሎምቢያ ምክትል የንግድ ሚኒስትር ሊዊስ ፊሊፔ ኬንቴሮ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሥራ ኃላፊዎችና የሁለቱ ሀገራት የቢዝነስ ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል:::

የሁለቱን ሀገራት የኢኮኖሚ ትስስር ለማሣደግ ሁለንተናዊ የዲፕሎማሲና የኢኮኖሚ ልውውጥን ከፍ ማድረግ እንደሚገባ በፎረሙ ላይ ተነስቷል።



ለኮሎምቢያ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ሥላለው የኢንቨሥትመንት እድል ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን የሁለቱ ሀገራት የቢዝነስ ተቋማት የቢዝነስ ለቢዝነሥ ውይይትም ተካሂዷል። የኮሎምቢያ ኩባንያዎችም ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር ለመሥራርት ፍላጎት እንዳላቸውም ገልጸዋል።

በአልጄሪያ አስተናጋጅነት "Gateway to New Opportunities" በሚል መሪ ቃል እየተካሄደ የሚገኘው እና በአልጄሪያ መንግስት፣ በAfrican Export-Import Bank (Afreximbank)፣ በአፍሪካ ህብረት ኮሚሽንና በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ሴክሬታሪያት ትብብር የተዘጋጀው 4ኛው የመላው አፍሪካ የንግድ ትርኢት የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችና ከፍተኛ ባለስልጣናት እንዲሁም የተለያዩ





ሀገራት ባለስልጣናትና የአህጉራዊ እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ኃላፊዎች በተገኙበት በክቡር የአልጄሪያ ፕሬዚዳንት አብዱልመጂድ ተቡን በይፋ ተከፍቷል።

የመክፈቻ ሥነ-ስርዓቱ በአልጄሪያው ዓለም ዓቀፍ የኮንፍረንስ ማዕከል የተደረገ ሲሆን የመሪዎች ራውንድ ቴብልም ተካሄዷል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኤምባሲ አልጀርስ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደርና ልዩ መልዕክተኛ የሆኑት ክቡር አምባሳደር ሙክታርን ጨምሮ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከፍተኛ አመራሮች የንግድ ቀጠናዊ ምንስቴር የዉጭ ጉዳይ ምንስቴርን ጨምሮ ልዑካን ቡድኑ በመክፈቻ ሥነ-ስርዓቱ ላይ ኢትዮጵያን ወክለው ታድመዋል።






የአገራችን ልዑክ ቡድን ከ16 የሀገራችን ካምፓኒዎች የተውጣጡ ከ45 በላይ ተሳታፊዎችን ያቀፈ ሲሆን በቡና፣ በጨርቃ ጨርቅ፣ Agro-Processing፣ በስጋ፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች እንዲሁም ቅመማ ቅመም ዘርፍ ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን ለአልጄሪያ እና ከሌሎች የአፍሪካ እንዲሁም የዓለም አገራት መጥተው ለሚሳተፉ የንግድ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚያስተዋውቁ ሲሆን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ትስስርም ለመፍጠር የሚችሉበት መልካም አጋጣሚ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በንግድ ትርኢቱ ላይ ከ140 ሀገራት የተውጣጡ ከ2000 በላይ ኩባንያዎች ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሲሆን ከ35,000 በላይ ፕሮፌሽናል ባለሙያዎች ጉብኝት እንደሚያደርጉ እና በዚህም 44 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ የንግድና ኢንቨስትመንት ስምምነቶች የሚፈረሙበት እንደሆነም ይጠበቃል።

ከዚህ አንፃር የሀገራችን የቢዝነስ ልዑክ በንግድ ትርኢቱ ላይ በሚካሄዱ የቢዝነስ ለቢዝነስ ግንኙነቶች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ከመጡ ገዢዎችና ሻጮች ጋር ትስስር የሚፈጥርበት ትልቅ ዕድል የሚፈጥር መድረክ ይሆናል።





IATF የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ1963 ሲመሰረት እንዲቋቋም የታሰበ ቢሆንም እውን የሆነው በ2017 ሲሆን የመጀመሪያ ትርኢቱን በ2018 በግብጽ አስተናጋጅነት አካሂዷል። የቀጣዩን እና 5ኛውን የIATF መርሃ ግብር ናይጄሪያ ከ ሁለት ዓመታት በኋላ ለማዘጋጀት እድሉን መውሰዷን በመክፈቻ መድርኩ ላይ ተገልጿል። IATF የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ተቋም ሆኖ ቋሚ መስሪያ ቤቱን በዚምባቢዌ እንደሚያደርግም በመድረኩ ላይ ተገልጿል።

በአልጄሪያ- አልጀርስ እየተካሄደ ባለው 4ኛው የመላው አፍሪካ የንግድ ትርኢት (IATF) ላይ እየተሳተፈ ያለው ፤ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የተመራው የልዑካን ቡድን ከአልጄርያ የንግድና እንዳስትሪ ም/ቤት ፕሬዝዳንት ሚ/ር ከማል ሃመንኢ ጋር ተወያየ።



መምከራቸውንና በቀጣይ በሚሰሩ ጉዳዮች ላይ ከመግባባት ላይ



በውይይቱም ሁለቱ ም/ቤቶች በጋራ ሊያከናውኗቸው በሚገቡ እንዲሁም የሁለቱን አገራት የንግድ ማህበረሰብ በማቀራረብ በጋራ በሚሰሩ ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ መደረሱን ፕሬዚደንቱ ገልፀዋል።



4ኛው የመላ አፍሪካ የንግድ ትርኢት (IATF) በአልጄሪያ አልጀርስ ከተማ በደማቅ ሁኔታ ለሁለተኛ ቀን ሲቀጥል የኢትዮጵያ ፓቪሊዮን ላይ ከፍተኛ ጎብኝዎች እየተመዝገቡ ስለመሆኑም በቦታው የሚገኙት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገልፀዋል ::







የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አፍሪካ ኢን ሞሽን (Africa in Motion) ከተሠኘ ተቋም ጋር የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራረመ። ሁለቱ ተቋማት በተለይም በአቅም ግንባታ፣ በሥልጠና፣ በወጣቶች፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ዙሪያ እንደሚሠሩ ተጠቁሟል።



የሥምምነት ፊርማውን የተፈራረሙት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር)፣ የአፍሪካ ኢን ሞሽን ዳይሬክተር ማክሥ ኮፊ እና የኢኳል ትሬድ ዎሜን አሊያንሥ (Equal Trade Women Alliance) ኃላፊ ወይዘሮ እንግዳየ እሸቴ ናቸው።



የተፈረመውን የሥምምነት ሠነድ ወደ ተግባር በመቀየር በኢትዮጵያ በቴክኖሎጅ የተደገፈ የአቅም ግንባታ፣ አድቮኬሲ፣ በወጣቶችና ሴቶች እንዲሁም በቢዝነሱ ውስጥ ልማት ላይ በቁርጠኝነት መሥራት ያሉ አካል ጉዳተኞችን ለመደገፍና በኢትዮጵያ የባህልና ቱሪዝም እንደሚገባ ተነስቷል።

አፍሪካ ኢን ሞሽን በአፍሪካ ማህበረ- ኢኮኖሚያዊ ችግሮን በማስተሳሰር መፍተሄ ማምጣት ብሎም በኢኳል ትሬድ አቅም ማሳደግ እና በዓለም የንግድ ሂደት ውስጥ የአፍሪካን የሚሰራ ነው።

ለመቅረፍና ከአውሮፓ ጋር አሊያንስ በኩል በአካባቢያዊ አበርክቶ ማሳየት ላይ በማትኮር

በሥምምነት ስነ ስርዓቱም የአፍሪካ ኢን ሞሽን ካንትሪ ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ወልደሠማያትን ጨምሮ ባለድርሻ አካላት እና ሌሎች የምክር ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የኔዘርላንድስ ልማት ድርጅት(SNV) በትብብር ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ።



የመግባቢያ ሰነዱ የተፈረመው በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና መስሪያ ቤት ሲሆን የመግባቢያ ስምምነቱን የተፈራረሙት የም/ቤቱ ዋና ፀሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና የኤስኤንቪ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ጁሊ ግራሃም ናቸው።



ሁለቱ ተፈራራሚ ወገኖች በቀጣይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በ አ ዲ ቮ ኬ ሲ ፣ እና ጥቃቅን እና

እንዴት በጋራ መስራት እንደሚችሉ ተወያይተዋል፤ በውይይታቸውም ዲጂታላይዜሽን፣ የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ ወጣቶችና ሴቶችን ማብቃት አነስተኛ ኢንትረፕራይዞችን መደገፍ ላይ በጋራ ለመስራት ተስማምተዋል። በፊርማ ስነ ስርዓቱ ላይ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሀፊ የስልጠና ቁ ሳ ቁ ሶ ች ን





ተረክብለዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) በኢትዮጵያ የኮሎምቢያ ሪፐብሊክ አምባሣደር የሰን አርካዲዮ ሜኔሴስ ጋር ተወያዩ።



ኮሎምቢያ በአዲስ አበባ ኤምባሲዋን መክፈቷ በሀገራቱ መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ትብብር ለማጠናከር ትልቅ አሥተዋጽኦ እንዳለውም ተጠቁሟል።ሁለቱ አካላት በኢትዮጵያ እና ኮሎምቢያ በኩል ባሉ የንግድና ኢንቨሥትመንት እድሎች ዙሪያ ተወያይተዋል።



በውይይታቸውም ቀጣይነት ባለው መልኩ ያሉ እድሎችን ለመጠቀም በትብብርና በጋራ እንደሚሠሩ ተጠቁሟል።





በኦሮሚያ የተለያዩ ከተሞች የተካሄደ ነዉ። ከከተሞቹም መካከል ጅማ፥ አሰላ፥ ሻሸመኔ እና ወሊሶ ከተሞች ይገኙበታል።

በጅማ ዞን ለግብርና ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን ለማምረት መቻሉን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ



ገመቹ ኤግዚቢሽኑን በከፈቱበት ወቅት አስታውቀዋል። በዞኑ የተመረቱ የግብርና ምርቶች ለሃገር ውስጥ ፍጆታ አልፈው ለውጭ ገበያ እየቀረቡ መሆኑንም ተናግረዋል።



በኤግዚቢሽኑ ጅማ እና አካባቢዋ የሚመረቱ የግብርና ውጤቶች፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲሁም የባሕል አልባሳት እና በእጅ የተቀረፁ ቅርፃ ቅርፆች ለገበያ ቀርበዋል። ኤግዚቢሽኑ በጅማ ዞን እና በከተማው ንግድ ፅሕፈት ቤት ቅንጅት የተዘጋጀ ሲሆን ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት የሚቆይ ይሆናል።(ምንጭ፥ ኦሮሚያ ንግድ ምክር ቤት እና ኢቢሲ)

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከስራና ክህሎት ሚንስቴር ጋር በመተባበር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የግሉ ዘርፍ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማፍራት ላይ አትኩረው እንዲሰሩ





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከስራና ክህሎት ሚንስቴር ጋር በመተባበር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የግሉ ዘርፍ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማፍራት ላይ አትኩረው እንዲሰሩ የሚያስተባብር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማስተባበርያ የስራ ክፍል (TVET Coordination Unit) በGIZ –STEP IV ፕሮጀክት የቴክኒክና ፋይናንስ ድጋፍ በማቋቋም ላይ ነው።

የማስተባበርያ ስራ ክፍሉ ዋና ዓላማ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰው ኃይል እንዲያመርት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማጎልበት ነው።





የማስተባበርያ ክፍሉን ማቋቋም አስፈላጊነትና ትግበራውን በተመለከተ በዛሬው ዕለት አስፈላጊ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሳፋየር አዲስ ሆቴል የምክክር መድረክ ተካሂዷል።

በአስፈላጊነቱና አተገባበሩም ላይ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክትል ዋና ፀሐፊ አቶ ፀደቀ ድጋፌ፣ በስራና ክህሎት ሚ/ር የሙያ ደረጃና ስርዐት ስልትና ዝግጅት እና ብቃትና ምዘና መሪ ስራ አስኪያጅ ወ/ሮ ማርታ ወልዴ እንዲሁም በGIZ STEP IV ፕሮጀክት የግሉ ዘርፍ አማካሪ ወ/ሮ ሰብለወንጌል ሀረገወይን የመወያያ መነሻ ሀሳቦችን አቅርበዋል፤ ከባለድርሻ አካላት ለተነሱ ጥያቄዎችም ምላሽና ማብራርያ ሰጥተዋል።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከኦማን ሱልጣኔት ከመጡ ኩባንያዎች ተወካዮች ጋር ተወያዩ።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከኦማን ሱልጣኔት ከመጡ ኩባንያዎች ተወካዮች ጋር ተወያዩ።



ዋና ጸሐፊው በውይይታቸውም በኢትዮጵያ ስላሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች እንዲሁም የንግድ ምክር ቤቱ በሚሰራቸው ዋና ዋና ተግባራት ዙሪያ ገለጻ አድርገውላቸዋል።

ኩባንያዎቹ አልራፋ ኢትዮጵያ አር እና አር ትሬዲንግና ኢንቨስትመንት ኃ/የተ//የግል ማህበር ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ በተለይም የቁም እንስሳትን ወደ ውጭ በመላክ እና በስጋ ማቀነባበር ዘርፍ ላይ ለመስራትና በኢንቨስትመንት የመሰማራት ፍላጎት እንዳላቸውም ጠቁመዋል።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) ከኦሮ ኮንስትራክሽን ግሩፕ ዋና ስራ አሥፈጻሚ ዶክተር ኢንጅነር መሣይ ዳንኤል ጋር ተወያዩ።



የሥራ ኃላፊዎቹ ሁለቱ ተቋማት በትብብር እና በጋራ በሚሠሩባቸው ዘርፎች ላይ መክረዋል።

ኦሮ ኮንስትራክሽን ግሩፕ በግንባታው ዘርፍ ያለውን አቅም በማጎልበት ላይ የሚገኝ ድርጅት ሲሆን ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በአቅም ግንባታ ሥልጠና እና በሌሎችም ዘርፎች በትብብር እንደሚሠራ ተጠቁሟል።

ምክር ቤቱም በተለይም በቢዝነስ ሊደርሺፕ አካደሚ የሥልጠና ማዕከሉ በኩል ሠፊ የሥልጠና እድል እንዳለውና ከግሩፑ ጋር መሥራት እንደሚፈልግም ተገልጿል።



የአፍሪካን ልማት ለማምጣት ያለን አቅም ማወቅና ትብብርን ማጠናከር እንደሚገባ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ገለጹ።



የአፍሪካን ልማት ለማምጣት ያለን አቅም ማወቅና ትብብርን ማጠናከር እንደሚገባ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ገለጹ።



ዋና ጸሀፊው ይህንን ያሉት መቀመጫውን ጋና፣ አክራ ካደረገው ቦልድ ሶሉሽንስ ግሩፕ ከተሰኘው ተቋም ዋና ስራ አስፈጻሚ ፔሸንስ ናዲ አንዶህ ጋር በትብብር ሊሰሩ በሚችሉ ጉዳዮች በማዘጋጀት የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች፣ በያዝነው የነሀሴ ወርም በአዲስ እንደ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ እና ሴራሊዮን ባሉ ሀገራት አጋር ያሉት አፍሪካዊ ተቋም ነው።

በተወያዩበት ወቅት ነው። በውይይታቸውም በግሩፑ እና በምክር ቤቱ መካከል ዙሪያ መክረዋል።

ቦልድ ሶሉሽንስ ግሮፕ አፍሪካ አቀፍ እና ክፍለ አህጉራዊ የልማት ጉባኤዎችን የልማት አጋሮች እና ሌሎች አካላት በትብብር መስራት እንዲችሉ የሚሰራ ሲሆን አበባ ጉባኤውን አካሂዷል። መቀመጫውን ጋና ያደረገው ቦልድ ሶሉሽንስ ግሮፕ ሴራሊዮን ባሉ ሀገራት አጋር ያሉት አፍሪካዊ ተቋም ነው።

"የኢትዮጵያን ይግዙ" 3ኛው ሲዲ-ቻምበር 2018 አዲስ ዓመት ዋዜማ ኤግዚብሽን እና ባዛር በሐዋሳ ከተማ ተካሄደ።



ኤግዚቢሽንና ባዛሩ የሲዳማ ክልል የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከሲዳማ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ እንዲሁም ከቢኒያም ፕሮሞሽን ሰርቪስ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው።

በመክፈቻ ስነ ስርዓቱም የክልሉን ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ፣ የዞን አስተዳዳሪዎች፣ የምክር ቤቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ጨምሮ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ እንግዶች እና የሐዋሳ ከተማ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።



በዚህ ዝግጅት ከ3 መቶ በላይ ተቋማት ተሳታፊ ሲሆኑ ኢትዮጵያ ኮርፖሬሽንን ጨምሮ የመንግስት ድርጅቶች፣ ቡና ላኪዎች፣ የቸርቻሮ ነጋዴዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ማህበራት እና የተለያዩ እንዱስትሪዎች ተሳትፈዋል።



በኤግዚቢሽኑ የይርጋዓለም አግሮ እንዱስትሪ ፓርክ ውጤቶችን ጨምሮ የተቋማት የተለያዩ ምርቶች፣ የበቆሎ፣ የስዴ እና የጤፍ እንዲሁም ሌሎች የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለግብይት ቀርበዋል። ኤግዚቢሽንና ባዛሩም ከነሐሴ 17 እስከ ጳጉሜ 05/2017 ዓ.ም ክፍት ሆኖ እንደሚቆይ ታውቋል።

ነሃሴ 22 /2017 የትግራይ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የመንግስትና የግል ሴክተር ምክክር መድረክ PPD በመቐለ ከተማ አካሄደዋል ።



ነሃሴ 22 /2017 የትግራይ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የመንግስትና የግል ሴክተር ምክክር መድረክ PPD በመቐለ ከተማ አካሄደዋል ።

የምክክር መድርኩን የክልሉ ጊዝያዊ መስተዳደር ፕረዚደንት፣ የክልሉ

የኢንቨስትመንት ኮምሽን ኮሚሽነር እና የክልሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር



ቤት ፕረዚደንት በጋራ የመሩት ሲሆን በምክክር መድረኩ

የክልሉ የካቢኔ አባላት ፣ የመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት፣



ባንኮችና የፋይናንስ ድርጅቶች እንዲሁም ከክልሉ የተውጣጡ ባለሃብቶች

እና ባለ ድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

በምክክር መድረኩ ለንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ማነቆ የሆኑ ችግሮች የተነሱ ሲሆን ምክክር ተደርጎባቸው፣ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥና የትግበራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር እንዲገባ በክልሉ ግዜያዊ አስተዳደር ፕረዝደንት አቅጣጫ ተሰቶበታል::

በኢትዮጵያ ፣በጂቡቱና በአፍሪካ ህብረት የኢንዶኔዢያ አምባሳደር ፋይዛል ቼሪ ሲድሃርታ የተመራ የልዑካን ቡድን አርባ ምንጭ ከተማ ገብተዋል::



የልዑካን ቡድኑ አርባ ምንጭ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲደርሱ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ቦጋለ ቢታኔን ጨምሮ የክልልና የዞን የስራ ኃላፊዎች ፣ የጋሞ አባቶች አቀባበል አድርገውላቸዋል።



ልዑካኑ በቆይታቸው በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና በአርባ ምንጭ ከተማ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አስተባባሪነት በንግድ ለንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ዙሪያ ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በአርባ ምንጭ ከተማ በሚካሄደው የምክክር መድረክ ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል በሚደረጉ ምክክሮች (Public - Private Dialogue) ስምምነት ላይ በተደረሠባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተካሄደ!





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ከግብርና ሚኒስቴር ከተውጣጡ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ነው ውይይት የተካሄደው።

በግብርና ምርቶች እሴት ስንሰለት እንዲሁም የገበያ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ምክክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል።



በአሁኑ ወቅትም በግብርና ምርቶች የእሴት ሠንሠለት ዙሪያ የሚታዩ ተግዳሮቶችእና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ የተገኙ ውጤቶችና በቀጣይም የግብርና ምርቶች ከአመራረት፣ ከመረጃ እና ግብዓት እሥከ ዓለም አቀፍ ገበያ ድረሥ ያሉ የእሴት ሠንሠለት ስራዎች (Value chain) በውይይቱ ተዳሠዋል።

የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ የተጀመረው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርድ ማኅበራት ምክር ቤት ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን በ2002 ዓ.ም ነው። ባለፉት ዓመታትም በበርካታ ጉዳዮች ዙሪያ ምክክሮች ተደርገው በተገኘው ግብዓት መሠረት የተለያዩ የህግና አሠራር ማሻሻያዎች መደረጋቸው ይታወቃል።

የንግዱ ማህበረሰብ አንድ ወጥ የግብር ማኑዋል እንዲታተም ጠየቀ

የንግዱ ማህበረሰብ የአገሪቱን የንግድና የኢንቨስትመንት ከባቢ አየር ለማሻሻል የሚያስችሉ የግብር ማሻሻያዎችን አስመልክቶ ባቀረበው ጥሪ፣ ሁሉንም መመሪያዎች በአንድ ላይ ያካተተ አጠቃላይ የግብር ማኑዋል እንዲዘጋጅና እንዲታተም ጠይቋል።



ይህ ጥያቄ የቀረበው በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባዘጋጀው የመንግስትና የግል ውይይት (PPD) መድረክ ላይ ነው።

መድረኩ በኢትዮጵያ ያለውን የግብርና የጉምሩክ ስርዓት ለማሻሻል ያለመ ሲሆን፣ ከግል ዘርፉ የተውጣጡ ተወካዮች የግብር አሰባሰብ ስርዓቱ



በአግባቡ ለመፍታት እንደ መፍትሔ ያስቀመጠው፣ ሁሉንም ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአንድ ላይ በማሰባሰብ ግልጽና በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል ማኑዋል እንዲታተም ነው። ይህም የግብር ከፋዮችን ጊዜና ወጪ ከመቆጠብ በተጨማሪ፣ ግብር የመክፈል ፍላጎትንና ተገዥነትን ከፍ እንደሚያደርግ ተጠቁሟል።

ውስብስብና ለመረዳት አስቸጋሪ መሆኑን አንስተዋል።

የግብር መመሪያዎችና ህጎች በተለያዩ ሰነዶችና ጊዜያት የሚወጡ በመሆናቸው፣ ግብር ከፋዮች ለመረጃ ለመድረስና ግዴታቸውን ለመወጣት እንደሚቸገሩ ገልጸዋል። የግሉ ዘርፍ ይህንን ችግር

የበሻሻ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በጅማ ዞን ጉማይ ወረዳ ኤፎ ያጪ ቀበሌ ለሚኖሩ አቅመ ደካሞች የበጎ ስራ አገልግሎት አከናውኗል።





የበሻሻ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መሀመድ አወል ሰይፉ እንደገለፁት ምክር ቤቱ በዛሬው ውሎው ለአቅመ ደካሞች የመኖሪያ ቤት የማደስ እና የማሰራት ተግባር አስጀምሯል።

በቦታው የምክር ቤቱ ሙሉ የቦርድ አባላት የተገኙ ሲሆን ፤በዕለቱም የወረዳው አስተዳድር አቶ ሚፍታ አ/ዱራ ለምክር ቤቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል ፤ እንዲህ አይነት ተግባራት ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል።





የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት







የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች

ራዕይ

“በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት”

ተልዕኮ

“የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት”

ዕሴቶች

- ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ኃላፊነት

ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካትት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)

ዋና አዘጋጅ፡-

ተሾመ ዋቅጂራ

ም/ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ

ስማቸው ተበጀ

ፎቶግራፍ

ያለምፍሬ በቀለ



The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)

ስልክ: +251115514005

ፋክስ: + 251115517699

P. O. Box 517,

ኢ.ሜይል: info@ethiopianchamber.com

ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com

ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber

ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber

ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA

Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in